በስደት ከኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

## የሰሞኑ የወያኔ ድራማ በመመህራን ዙሪያ፦መምህራን የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው እንዳይሆን እንጠንቀቅ !!

ያሁኑን የጥፋት ዘመን አያድርገውና መምህራን የብዙ መልካም ነገሮች ተምሣሌት ሆነው ቅጥያ ስም እየተጣቸው ቆይተዋል ።ለህልውና እጅግ በጣም አስፈላጊ በሆነው ፤ ደምን በሰውነት በሚያሰራጨው ልብ ተመስለዋል።መምህሩ ለሃገሩ እንደ ልብ ነው ግብሩ(As the heart is to the body; The teacher is to the nation) ተብሎ ሲነገር ነበር። እንዲያውም ይህ የልብ ተግባር ለሕይወት ወሳኝነት ያለው ከመሆኑ ባሻገር አንዳንድ ጊዜ የአእምሮን ተግባር የመተካት ያህል ልባዊ፡ልባም፤ልበቢስ፤ልበሙሉ...... በሚሉ ቃላት እየተገለጸ ተግባሩና ግዳጁ ከፍተኛ እንደሆነ የሚነገርበት አጋጣሚም አለ።ይህ መምህራን ለአንድ አገር ዕድገትና ብልጽግና የሚያበረክቱት ግልጋሎት ዙሪያ ገብ እንደሆነ ያሳያል።

መምህራን ድንቁርናን በማስውገድ ፤የማህይምነትን ጥቁር መጋርጃ መግፈፍ ብቻ ሳይሆን የሕብርተሰብ ዕድገት በላቀ ደረጃ እንዲደርስ ሙያዊ ግዴታና ኃላፊነትም ስላለባቸው እየቀለጠች ብርሃን በምትሰጠው ሻማም ይመሰላሉ።

ማስተማር ክቡር ሙያ ነው (Teaching is the noblest Profession of all trades) እየተባለም ተነግሮለታል። በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ማህበራዊ ሥፍራ ከበሬታ የተቸረው ስለነበር ለጋብቻ የሚመረጥ መሆኑን ለማሳየት በሠርግ ወቅት " የእኛ ሙሽራ ሹራብ ሰሪ ወሰዳት አስተማሪ" የሚለው ዜማ ዳስ ማድመቂያ ሆኖ ይሰማም ነበር።ሱፍ አማርጠው ከሚለብሱት ከተሜዎች መምህራን ከመጀመሪያው ረድፍ የሚታወቁ ነበር።

በገጠርም ሆነ በከተማ ለዓምት በዓል ገቢያ ሲወጡ ምርጥ ሙክትና መሲና እንዲሁም በጋራ እየሁኑ ሽህርና ሡንጋውን ለመግዛት የሚቀድሟቸው ካሉ እጅግ ጥቂቶች ይሆናሉ ። ለዚህ ያበቃቸው በወቅቱ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ደረጃና የሚያበረክቱት ግልጋሎት የሰውን ልጅ በዕውቀት መቅረጽና መገንባት መሆኑ ታምኖበት በቂ ነው ተብሎ የሚጋነን ባይሆኑም የተሻለ ደሞዝ ስለሚከፈላቸው ነበር፤ወደሙያው የሚገቡትም ሕብረተሰቡ ለሙያው በሚያሳየው ከበሬታና ከሌሎች የሚኒስቴር መ/ቤቶች ከአየር መንገድ፤ባንክና ኢንሹራንስ ከመሳሰሉት በቀር በአንፃራዊ ሲታይ የተሻለ ክፍያ መስጠቱ ፤ሙያው ተወዳጅም ተፈላጊም ነበር። ማህበራዊ ከበሬታውም ከፍ ያለ ነበር። በሙያውም ከተሰማሩ በኋላም በሥልጠና ወቅት ባገኙት ዕውቀትና ሙያዊ ሥነ ምግባር (ኤቲክስ) በመታገዝ ጦር ግንባር እንደተሰለፈ ጀግና ወታደር ኋላቀርነትን፤ድንቁርናን፤ማይምነትን፤ፍትህ መጓደልን ፤ ብዝበዛን......... በጣምራ እየታገሉ ፤ እያስተማሩ ብሔራዊና ሙያዊ ግዴታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል። በጣም የሚገርመው መምህራን "ለራሴ" ብለው የሚስገበገቡበትና የሚያማምላቸው ቁሳዊ ሀብት

የሚታያቸው አልነበረም ። የሚያገኙት ሐሴት ቢኖር ያስተማሯቸው ወጣቶች ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሰው ማየት እንጂ።

በማስተማር ሙያ ለመሰማራት የሚታሰበው ሥራ ከማግኘት በተጨማሪ በማህበረሰቡ ያለውን ተቀባይነት ስለሚዊዱት ከዚያም በላይ አገርቸውን በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሥልጣኔ ተቋዳሽ እንድትሆን ከልብ በማመንና በተግባርም ለማሳየት ነው። ወደ ማስተማር ሙያ የሚገባ የምልመላው ዋልታና ማገር ሙሉ ፈቃደኝነትን፤አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ክህሎትን ፤ አምራችና ተመራማሪ ትውልድ የማፍራት ዝንባሌና ችሎታን ፤ ማህበራዊ'ባህላዊና ሞራላዊ እሴቶችን የመጠብቅ ኃላፊነት መሸከምን፤ ....... የሚያጠቃልል ነው።

በአሁኑ ጊዜ እንዚህና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ወደጎን ተገፍተው በወያኔ በሚመራ እንድ ፓርቲ የፖለቲካ አጀንዳ አምኖ ያልተቀበለ ከሆነ ልዩ ተሰጥኦ ያለው ቢሆንም እንኳ በውድድሩ ተሳታፊ ሊሆን አይችልም ቢወዳደርም የመመረጥ ተስፋ አይኖረውም። ይህ እንዳለ ሆኖ አብዛኛዎቹ ነባርም ሆኑ የቅርብ ጊዜ ተቀጣሪ መምህራን ለሥርዓቱ የዘረኝነት ፖሊሲ የሚመቹ ባለመሆናቸው ለጥቃት ተጋልጠዋል። በመምህራንና በሙያ ማህበራቸው ላይ ሰለደረሰውና እስካሁንም ሳያቋርጥ ስለሚፈጸመው ሁለገብ ጥቃት በተለያዩ አጋጣሚዎች የኢመማ ፤ የስብአዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅቶች ፤ አለም አቀፍ የሙያና የሠራተኛ ማህበራት ፤ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ፤ እንዲሁም ግለሰቦች ያወጧቸው መግለጫዎችና የቀረቡ አስተያየቶች ከበቂ በላይ ግንዛቤ አስጨብጠዋል።

በዚህ አንፃር መምህራን ራሳቸውን ፤ማህበራቸውንና ሙያቸውን ነፃ ለማውጣት ያካሄዱት ትግልና የተከፈለው መስዋዕትነት ቀላል አልነበረም።ችግሩ ይህን የጥፋት ዘመቻ አንድ ቦታ ላይ ማቆም ያለመቻል ነው።ባለፈው ሕዳር ወር 2004 ዓ.ም መምህር የኔሰው ገብሬ ራሱን አንድዶ መስዋዕት ለመሆን እዚህ ውሣኔ ላይ የደረሰው የተቀናጀና የማያዳግም ርምጃ ለመውሰድና አምባገነኖችን በጋራ በቃችሁ ለማለት ያለመቻሉን ተገንዝቦ ነው ቢባል ከዕውነት መራቅ አይሆንም።

ወደ አንድነት ለመምጣትና ጠላትን ማንበርከክ ያልተቻለበት ምክንያት ብዙ ሊሆን ይችላል፡ በዘረኝነት ላይ የተተከለ ሥርዓት ዳፋው ይኸን ክቡር የሆነውን በአንድነት የመቆምን ዓላማ ማዳከም እንደሆነ በነዚህ ሃያ የመከራ አመታት የታየ ሃቅ ነው። ነገር ግን ሁሉም ምክኒያቶች ተደማምረው ይህን የለየት ግፈኛ ሥራዓት ለማስወገድ በጋራ መቆምን የሚያለመልሙ አይደሉም፤ አይሆኑምም። ምርጫው የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ሆኗል። ከዚህም በላይ የአገር ሕልውናና የዜግነት ጥያቄ ነው። ይህ በመንግሥት ስም ተቀምጦ የሕዝብን የበላይነት የገሠሠ ዘርኛ ቡድን ከተፈጥሮ ባሕሪውና ከሚያስየው እኩይ ተግባር አንፃር በድርድርና በመለመማጥ የመምህራንን ጥያቄ ይመልሳል የሚል ተስፋ ከቶውንም አይታይም።

ከሠራተኛ ጋር የመደራደር ነፃነትን (Freedom of bargaining)፤ በነፃነት መደራጀትንም (Freedom of Association) የመሳሰሉትን ዓለም አቀፍ ሕግጋትን የሚያከብር ቢሆን ኖሮ

ተለጣፊዎችን በአምሳያው ጠፍጥፎ መፍጠር ባላስፈለገው ነበር ። ይሁንና ወያኔ ለዚህ ፍትሐዊ አካሄድ አልታደለም። ይልቁንስ ባለሙያውን እንደኩሊ ቆጥሮ ባንድቀን ጀምበር ብዙዎችን ከሥራ የሚያባርርና የሚያፈናቅል፤በግዴታ አባሎቼ ሁኑ ብሎ ሰነድ የሚያድል ፤ መምህራንን በክረምቱ የዕረፍት ጊዜአቸውን በተጽዕኖ ለዘርኛ ፖለቲካ ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ጥምቀት የሚያግት፤ ብዙዎችን ከዕድገት፤ከትምህርትዕድል ፤ ከደሞዝ እስኬል ማስተካከያ ፤ ........ የሚያገል ሥርዓት በምን መለኪያ የመንግሥትነት ባሕርይ ሊገለጽ ይችላል ? መምህራን በአገዛዙ እየተፈጸመባቸው ባለው ጫና ሰለሙያቸው ፤ ስለ ማህበራቸው ፤ ስለትምህርት ጉዳይ፤ ባጠቃላይ በማህበራዊና አገራዊ አጀንዳዎች ቀጥተኛ ተሳታፊና ተዋናይም እንዳይሆኑ እግር ተወርች ታሥረዋል።ይህንን ጫና ተቋቁሞ ነፃ ለመውጣት የመምህራኑ የሥራ መስክና ጠባይ ይመቻል። አቅሙና ችሎታው፤ግንዛቤውም አላቸው። በዙሪያቸው የሚያሰልፉትም አጋር ኃይል ወሳኝነት ያለውና በተለይም ወጣቱን፤ ወላጆችንና ሌላውንም የህብርተሰብ ክፍል የሚያካትት በመሆኑ ከታጠቀ ሠራዊትም በላይ ለድል የሚያበቃ ኃይል ነው። ይህ እንዲህ ከሆነ ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይርዳም ነውና የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ መምህራን በቁርጠኝነትና በአንድነት ድምጻቸውን ሊያሰሙ ይገባል።

በሰሞኑ በአንዳንድ የአገሪቱ ክልሎች የታየው የመምህራን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ይበል የሚያሰኝ እንደሆነ ይሰማናል። መምህራን የቆየ ታሪካቸውን አድሰው እምቢ ባይነትን አንግበው ከተነሱ የድል ባለቤት እንድሚሆኑ አያጠራጥርም።ወትሮ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት አዲስ አበባ ተፈሪ መኮንን 2ኛ ደርጃ ወይም ልዑል መኮንን ፤ ደሴ ወ/ሮ ስኂን ፤ ሐረር መድኃኔአለም ፤ብቻ አንድ ቦታ ተቃውሞ ሲነሳ ትግሉን ሁሉም ይቀባበሉት ነበር። ያ ታሪክ በወያኔው የጎሳ ፖለቲካ የመለያየት ድባብ አጥልቶበት ቢቆይም አሁን አሁን ሕዝቡ ሐቁን እየተረዳና የሥርዓቱን መሠሪ ተግባር አውቆ ወደጋራ ራዕይ እየመጣ ለመሆኑ ምልክቶች ጎልተው ወጥተዋል።ወደፊትም ይታያሉ።

መምህራን ለጎሳ ፖለቲካ እጅ አንሰጥም ፤የሚያስተሳስረን ሙያችን ንው፤በነፃ የመደራጀት መብታችን ይከበር፤ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በዕኩልነት፤ትምህርት በህዝብ ቁጥጥር ሥር ይዋል በማለታቸው ነበር የዘረኞች ዒላማ ሆነው የቆዩት።እዚህ ላይ ለማለት የታሰበው የሰሞኑ የአንዳንድ ክልሎች መምህራን የሙብት ጥያቄ የመላው አገሪቱ መምህራን ጥያቄ አካል በመሆኑ መቀናጀትና እንቅስቃሴውም በጋራ መስተጋብባት ያለበትና እስከድልም የሚያበቃ ሊሆን እንደሚገባ ለማመልከት ነው።ከጠላት ጎራ የሚኾጎደጎደውን የመከፋፈል ፕሮፖጋንዳ ከመቋቋም አልፎ ለመስዋዕትነት መዘጋጀትንም ይጠይቃል።ወሳኙ የእኛ የመምህራን ጥንካሬና አንድነት ነው እንጂ የጠላት ድንፋታና ማስፈራሪያ፤የአጋዚም ጋጋታ አለመሆኑን መናገር ይቻላል።እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው አንድ ዋነኛ ቁም ነገር የመምህራንን የሙብት ጥያቄ አንስቶ እንድሚሟገት የሚነገርለት “ተለጣፊ” በመባል የሚታወቀው የወያኔ ማህበር የምር የመምህራንን ብሶት አስተጋብቶና አጠናክሮ እልባት ሊያስገኝለት ይቆማል ወይ ነው። የመላ አገሪቱ መምህር መርጦ ያስቀመጣቸው መሪዎቹ በወያኔ ካድሬ መምህራን እንዲተኩ(እንዲሾሙ) ተደርገው ለፈጠራቸው ዘረኛና አፋኝ ሥርዕት አገልጋይ ሆነው መቆየታቸው የሚታወቅ ነው። በርግጥ ግፍና መከራው መምህራን

ከማይችሉበት ድረጃ በላይ በመውጣቱ የሚያሳዩትን እምቢተኛነት ተለጣፊው ማድበስበስና ማቆም ከማይችልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ ጥያቄውን ለማፈን ወደ ፈጣሪው ወደ ወያኔ ለመወርወር የተገደደ ይመስላል። ከተለጣፊው  የወያኔ መምህራን ማህበር ለመምህራን መብት ይቆማል ብሎ መጠበቅ "ከእባብ  ዕንቁላል እርግብን እንደመጠበቅ" ነው።

ከሕዝብ ጋር እልህ የተጋባው፤ከፍትህና ርትዕ የተጣላው ውያኔ ለመምህራን መብት ጥያቄ ቀናነት ያሳያል ተብሎ አይጠበቅም።ሊሆን የሚችለው ውያኔ እንደ ልማዱ የባስ ማወናበድና የማዳከም ተግባሩን መቀጠል አለበለዚያም ከዚህ በፊት በመምህራን ላይ ያደርስ ከነበረው የበለጠ ትርምስ መፍጠር ነው።ተለጣፊው ማህበር ይህንን ተቋቁሞ መምህራንን በአንድነት አሰባስቦ ለድል ሊያበቃው ቀርቶ የራሱ ተፈጥሮና ተግባሩ ለዚህ የሚያበቃ አይደለም። እየሆን ያለው ወያኔ በመምህራን ላይ ሌላ ወያኔአዊ ድራማ እያዘጋጁ መሆኑ ነው።በዚሁም ድራማ ተለጣፊው በመምህራን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድርግና ጠንካራና አገር ወዳድ መምህራንን በመለየት የጥቃታቸው ሰለባ ለማድርግ ነው።

መምህራን የወያኔን ሴራ በመረዳት  የሚያካሂዱት ትግል በደሞዝ ጭማሪ በቻ መታጠር የለበትም፡ይልቁንም የሀገራቸው ሕልውና አደጋ ላይ መውደቁን፤የሕዝቡም ነፃነት በሁሉም መልኩ መገፈፉን ቅድሚይያ በመስጠት፤በነፃነት መደራጀት፤የመደራደር፤ የሥራ ዋስትና ፤ የትምህርት ዕድልና ሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩላቸው መካተት ይኖርባቸዋል።የመምህራን ትግል ለማኮላሸት ወያኔ የተውኔቱን መቅድም ካድሬ መምህራንን አሰባስቦ ተለጣፊ ማህበሩ የተቃወመና የተለዩ ለማስመሰል ሃቀኛ መምህራንን ለማታለል እንዲያመቸው ተለጣፊ ማህበሩ ያነሳው የደሞዝ ጭማሪና የሥራ ማቆም ጥያቄ የእኛ ጥያቄ አይደለም እንዲሉ በማድረግ ላይ ነው። "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ"ማለት ይህቺ ናት። ወጣም ወረደ ቁልፉ ያለው በመምህሩ እጅ ነው።መምህራን በጋራ በመቆም፤ ማህበራቸውን ኢ. መ ማን ዕውን በማድረግ ፤ ከዚያም የመምህራንን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ሕዝባዊና አገራዊ አጀንዳዎችን በመጠየቅ ትግሉን አጠናከሮ ዳር በማድረስ አገርን፤ሕዝብንና መብትን ማስከበር ይቻላል።በዚህ ረገድ መምህራን ለሃገርና ለወገን ዘብ የመቆም ልምዳችን ተሸመድምዶ ለራሳችን መሆን አቅቶን "ያባይን ልጅ ውሃ ጠማው" እንዲሉ እንዳንሆን መጠንቀቅና ለማያዳግም ድል እንታገል።የተለመደውን የወያኔን ፅረ- ኢ.መማ ድርጊትንም(ድራማውንም) መቋቋም ያስፈልገናል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

የመምህራን መብት በትግላችን ይከበራል

ኢ.መማም በሀቀኛ መምህራን ትግል ዕውን ይሆናል

በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አሰባሳቢ ኮሚቴ

የካቲት 21,2004 ዓ.ም

ለተጨማሪ መረጃ  eta1941@yahoo.com